
| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "የ'አፓርትሀይድ' ፡ አስከሬን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይቀበራል !" |
| ደሆሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ነሐሴ ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2015-003 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

## ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

# የ"አፓርትሀይድ" ፡ አስከሬን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይቀበራል !



ማን ፡ ያምናል ፡ ... ፨ ትላንት ፡ በአረመኔያዊው ፡ የ"**አፓርትሀይድ**" ፡ ሥርዐት ፡ ስትሠቃይ ፡ የነበረች ፡ **ደቡብ ፡ አፍሪቃ** ፡ ዛሬ ፡ ሐራ ፡ እና ፡ እግዝእት ፡ ሀገር ፡ ኾና ፥ በነጻነት ፡ ትግሏ ፡ ዘመን ፥ እንደ ፡ **ኢትዮጵያ** ፡ ኹሉ ፥ የደረሰችላትን ፡ **ቻይና** ፥ በስሟ ፥ ርእሰ ፡ ሀገር ፡ **ሺ ፡ ዢን ፡ ፒንግን** ፡ ታላቁን ፡ የደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ ኰከብ ፡ ስትሸልም ፤ ባንጻሩ ፥ **የአፍሪቃ ፡ የነጻነት ፡ ተምሳሊት ፡ ኢትዮጵያ** ፡ ደግሞ ፡ ከ 1983 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፥ በኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የ"*አፓርትሀይድ*" ፡ ሥርዐት ፡ ሥር ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ስትማቅቅ ! ማን ፡ ያምናል ፡ ... ፨

ይህም ፡ ብቻ ፡ አይደል ! ዛሬ ፡ ደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ምኅጻረ ፡ ቃሉ ፡ "***BRICS**: **B**razil-**R**ussia-**I**ndia-**C**hina-**S**outh Africa*" ፡ የተባለው ፥ ወይም ፡ በዐማርኛ ፡ ምኅጻረ ፡ ቃሉ ፡ "***ብሩሀቻደ*** ፦ ***ብ**ራዚል-**ሩ**ስያ-**ሀ**ንድ-**ቻ**ይና-**ደ**ቡብ ፡ አፍሪቃ*" ፡ ልንለው ፡ የምንችለው ፡ የመንግሥታት ፡ ትብብር ፡ አባል ፡ ሀገር ፡ ኾና ፥ ኢትዮጵያንም ፡ ለአባል ፡ ሀገርነት ፡ ስትጋብዛት ፡ ማየት ፡ እጅጉን ፡ ያስገርማል ።

አርባ ፡ በላይ ፡ መንግሥታት ፡ የ"***ብሩሀቻደ***" ፡ አባል ፡ ለመኾን ፡ ፍላጎት ፡ ቢያሳዩም ፥ ስድስት ፡ ሀገሮች ፡ ብቻ ፡ ተጋብዘዋል ፤ እነዚህም ፥ **ኢትዮጵያ** ፣ **ግብጽ** ፣ **ኢራን** ፣ **ሳዑዲያ ፡ ዐረቢያ** ፣ **የተባበሩት ፡ የዐረብ ፡ ኢማራት** ፣ **አርጀንቲና** ፡ ናቸው ።

" *ምንም ፡ በሙቱ ፥ ዐራድማ ፡ ሸምቱ* " ፡ እንዲል ፡ ያገራችን ፡ ሰው ፥ ገልቱነት ፡ የነገሠባት ፡ የዛሬዪቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምኑንም ፡ ያኽል ፡ ብትጐሳቈል ፥ ሥልጡን ፡ መሠረቷን ፡ እና ፡ የዘለቄታ ፡ ተስፋዋን ፡ በማሰብ ፥ የ"***ብሩሀቻደ***" ፡ አባላት ፡ መንግሥታት ፡ ቀዳሚ ፡ ምርጫቸውን ፡ "***ኢትዮጵያ***" ፡ ብለዋል ።

ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ **ኩነተ ፡ ሥልጣኔ** ፡ ( ወይም ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ***Civilisation-State*** ) ፡ ከተባለው ፡ የሀገሮች ፡ ወገን ፡ የምትመደብ ፡ ኩነት ፡ ወይም ፡ መንግሥት ፡ ናት ። ይህም ፡ ማለት ፥ ራሷን ፡ በራሷ ፡ ሥልጣኔ ፥ በ**ሥልጡንሕዝብና** ፡ የሠራች ፡ ሀገር ፡ ማለት ፡ ነው ። እንደ ፡ ቻይና ፣ ኢራን ፡ (ፋርስ) ፡ ያሉ ፡ **ራሳቸውን ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኔያቸው ፡ የሠሩ ፡ እና ፡ እግዚእናቸውን ፡ አስከብረው ፡ የሐራነት ፡ ታሪክ ፡ ያላቸው ፡ ጥንታውያን ፡ ሀገሮች ፡ በጣት ፡ ይቈጠራሉ** ። ከአፍሪቃ ፡ ኅብረት ፡ 54 ፡ አባላት ፡ አህጉራት ፡ ውስጥ ፥ ኢትዮጵያ ፡ አንድያዋ ፡ ኩነተ ፡ ሥልጣኔ ፡ ናት ፤ ሌሎቹ ፡ ሀገሮች — ክብራቸው ፡ እንደተጠበቀ ፡ ኾኖ — ከቅኝ ፡ ግዛትነት ፡ ሐራነት ፡ ሲወጡ ፡ ያገኙትን ፡ ህልውና ፡ ያዙ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፥ ራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ ሥልጣኔ ፡ በሀገርነት ፡ ሠሩ ፡ አያሠኝም ። **የሥልጣኔ ፡ መሠረቱ ፡ የርትዕ ፡ አክብሮት ፡ ወንፈል ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አገላለጽ** ፦ "***የብጤን ፡ መብት ፡ አክብሮ ፡ የራስን ፡ መብት ፡ ማስከበር***" ፡ **የሚለው ፡ የሥልጡንሕዝብና ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ይህ ፡ የርትዕ ፡ አክብሮት ፡ ወንፈል ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ደረጃ ፡ የጸናውን ፡ ያኽል ፥ በመንግሥታትም ፡ ደረጃ ፡ ስለሚጸና ፥ ለዓለም ፡ ሰላምም ፡ መሠረት ፡ ይኾናል** ።

እነዚህ ፡ ወዳጆች ፡ ሀገሮች ፡ ይህን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ተከባሪነት ፡ ይወቁላት ፡ እንጂ ፥ ሌሎች ፡ በክፉ ፡ ዐይን ፡ የሚያይዋት ፡ የምልክዮሽ ፡ (የ"*imperialism*" ) ፡


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

ኀይሎች ፥ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት ፡ አማካይነት ፥ አኹንም ፦ "ኢትዮጵያን ፡ ካላፈረስናት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የምናልመው ፡ ልዕልናችን ፡ እውን ፡ አይኾንም !" በሚል ፡ ጽኑት ፥ የማይፈነቅሉት ፡ ድንጋይ ፡ የለም ። እስካኹን ፡ በሻዕቢያ ፣ በወያኔ ፣ በኦ.ነ.ግ ፣ ወዘተርፈ ፣ የሚፈጸመው ፡ ዘመቻ ፥ ኢትዮጵያን ፡ አደከማት ፡ እንጂ ፡ አላፈራረሳትም ። መሣሪያዎቹ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እየለተቱ ፡ ከሥራ ፡ ውጭ ፡ ወደ ፡ መኾኑ ፡ በሚያዘነብሉበት ፡ በዚህ ፡ ሰዓት ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከእንቅልፉ ፡ እንደባነነ ፡ አንበሳ ፡ በዐምሐራነቱ ፡ መንቀሳቀስ ፡ ሲዠምር ፥ እንሆ ፥ በምልክዮሽ ፡ ሰፈር ፡ ጭንቅ ፡ ኾኗል ፦ "ዐምሐራ ፡ ከተነሣማ ፡ ዐለቀ ፡ ነገር ! ዐምሐራን ፡ መከፋፈል ፡ አለብን !" ብለው ፡ ወስነዋል ።

በ"ዐምሐራ ፡ ፋሺስታዊ ፡ ብሔርተኛነት" ፡ የሚደመደም ፡ "ዐምሐራ ፡ ዘር ፡ ነው ፤ ዐምሐራ ፡ ነገድ ፡ ነው" ፡ የሚል ፡ ተረት ፡ ተረትን ፡ በማኅበራዊው ፡ ማወራኛ ፡ በሰፊው ፡ መንዛትን ፡ ተያይዘውታል ። "በዐምሐራ ፡ ላይ ፡ የዘር ፡ ማጥፋት ፡ ይፈጸማል ! ዐምሐራው ፡ የሚታገለው ፡ ለህልውናው ፡ ነው !" ፡ የሚለውን ፡ አስመሳይ ፡ ትርክት ፡ የዋሃኑ ፡ ምንም ፡ ሳያመዛዝኑ ፡ በደም ፡ ፍላት ፡ ብቻ ፡ እንዲቀበሉት ፥ የሕፃናት ፣ የሴቶች ፣ የአረጋውያን ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ ያፈሳሉ ። **ይህን ፡ የምልክዮሽን ፡ ፀረ-ሀገር ፡ ፍጹም ፡ አረመኔያዊ ፡ ወንጀል ፡ በሻዕቢያ ፡ እና ፡ በወያኔ ፡ በተደራጁ ፡ የኦ.ሕ.ዴ.ድ.-ኦ.ነ.ግ. ፡ ወንበዴዎች ፡ እንዲፈጸም ፡ በመደረጉ ፥ መላው ፡ የኦሮሞ ፡ ማኅበረሰብ ፡ ተጠላበት ።** በፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ የቅኝ ፡ ግዛት ፡ ወረራ ፡ ዘመንም ፡ ኾነ ፥ በሻዕቢያ-ወያኔ-ኦ.ነ.ግ. ፡ የተሐድሶ ፡ ቅኝ ፡ ግዛት ፡ ወረራ ፡ ዘመን ፥ **ዐምሐራ ፡ የተጨፈጨፈው ፡ "ሀገር ፡ ኢትዮጵያ"ን ፡ አላስነካም ፡ በማለቱ ፡ ነው ። የምልክዮሽ ፡ ስልት ፡ ዅል ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፡ "ባንድ ፡ ድንጋይ ፡ ኹለት ፡ ወፎችን ፡ መግደል" ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥** "በዐምሐራ ፡ ላይ ፡ የዘር ፡ ማጥፋት ፡ ይፈጸማል" ፡ የሚለውን ፡ የገነቷ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ ዅሉ ፡ ሳያጠይቅ ፡ እንዲቀበለውና ፦

- አንደኛ ፥ **በሕገ ፡ አራዊት ፡ "አፓርትሀይድ" ፡ ደንብ ፥ ምልክዮሽ ፡ በመደበለት ፡ "ክልል" ፡ ዐምሐራው ፡ እንዲወሰን ፡ እና ፡ ስለ ፡ ሌላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍል ፡ "አያገባኝም" ፡ እንዲል ፤**
- ኹለተኛ ፥ **"ክልል" ፡ ዅሉ ፡ ካጎራባች ፡ "ክልሎች" ፡ በግዛት ፡ ይገባኛል ፡ ከርከሬሻ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ሲደማማ ፡ እንዲኖር ፤**
- ሦስተኛ ፥ **በምልክዮሽ ፡ አደራዳሪነት ፡ ለሚቀርብለት ፡ የአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ባለቤት-አልቦ ፥ ውጥን-ቅጥ ፡ ተዳብሎ ፡ (confederation) ፡ ሐሳብ ፥ "ክልል" ፡ ዅሉ ፡ የሚከላከልበት ፡ ኀይልም ፡ ኾነ ፡ ኅብረት ፡ ዐጥቶ ፡ እና ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ እንዲቀበል ፤**
- መደምደሚያውን ፥ **ባለቤት ፡ የሌለውን ፡ የአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፡ ምልክዮሽ ፡ አላንዳች ፡ ጠያቂ ፡ ለዘለዓለም ፡ እየነጠቀ ፡ እና ፡ እየመዘበረ ፡ እንዲኖር** ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

ደግመን ፡ ደግመን ፡ እንናገረዋለን ፦ **ዐምሐራ ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ የሚገደለው ፡ "ሀገር ፡ ኢትዮጵያን ፡ አላስደፍርም !" ፡ በሚያሠኘው ፡ የሀገር ፡ ባለቤትነቱ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። የዐምሐራ ፡ ህልውና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ህልውና ፡ አይለይም ። ዐምሐራ ፡ የተነሣው ፡ ኢትዮጵያን ፡ ብሎ ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነት ፡ (citizenship)** [(1)] **፡ እንጂ ፥ "ዐምሐራ" ፡ ለሚባል ፡ ከኢትዮጵያዊነት ፡ ለተለየ ፡ የፈጠራ ፡ የነገድ ፡ ማንነት ፡ አይደለም ፤ "ዐምሐራ" ፡ የሚባል ፡ የነገድ ፡ አባት ፡ የለም ። "ዐምሐራ" ፥ ከ 3000 ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ አኵስም ፡ ላይ ፥ በኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሀገርነት ፡ የሠራው ፡ የመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ (citizenry) ፡ የግብር ፡ ስሙ ፡ በመኾኑ ፥ ከኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነት ፡ የጠበበ ፡ ማንነትም ፡ ኾነ ፡ ግዛት ፡ የለውም ፤ መላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የርሱ ፡ ናት ፤ ርሱም ፡ የመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነው ።**

**"የዐምሐራ ፡ ብሔርተኛነት" ፡ ማለት ደግሞ ፡ የስሕተት ፡ ስሕተት ፡ ነው ።** "ብሔር" ፡ የሚያመለክተው ፡ የቦታ ፡ ስፋትን ፣ ምድርን ፡ እንጂ ፡ የሕዝብ ፡ እና ፡ የምድር ፡ አንድነት ፡ የኾነውን ፡ ሀገርን ፡ አይደለም ። **"ዐም ፡ ሐራ"** ፡ ማለት ፥ በደረቅ ፡ ትርጓሜው ፦ **"ነጻ ፡ ሕዝብ"** ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ጠለቅ ፣ ረቀቅ ፡ ያለው ፡ ትርጓሜው ፡ ደግሞ ፥ **በርትዕ ፡ ሥልጣኔው ፡ ወይም ፡ በሥልጡንሕዝብናው ፡ ሀገር ፡**

---

1 በዘመናችን ፥ ከ"ዜግነት" ፡ ይልቅ ፡ "ሀገራዊነት" ፡ ማለቱ ፡ ይመረጣል ። "ዜጋ" ፡ ግእዝ ፡ "ዜገ" ፡ ወይም ፡ "ተገዛ" ፡ ካለው ፡ የተገኘ ፡ ስም ፡ ነው ፤ እንግሊዝኛ ፡ "subject" ፡ ይለዋል ። "ሀገራዊ" ፡ ደግሞ ፥ በስምነቱ ፡ የሀገር ፡ ባለቤት ፣ ሀገርን ፡ የሠራው ፡ ሕዝብ ፡ አባል ፡ ማለት ፡ ነው ፥ እንግሊዝኛም ፡ "citizen" ፡ ይለዋል ፤ በቅጽልነቱ ፡ ደግሞ ፥ የሀገር ፡ ማለት ፡ ነው ፥ እንግሊዝኛም ፡ "national" ፡ ወይም ፡ citizen" (adj.) ፡ ይለዋል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

**ኢትዮጵያን ፡ የሠራው ፣ በሕጉ ፡ በሥርዐቱ ፡ መንግሥትን ፡ ያነጸው ፡ እና ፡ ያጸናው ፣ በደሙ ፡ እና ፡ ባጥንቱ ፡ የሀገርን ፡ ዳር ፡ ድንበር ፡ ጠብቆ ፡ ያቈየው ፡ የኢትዮጵያዊው ፡ ሥልጡን ፡ ሕዝብ ፡ መጠሪያ ፡ ነው ።**

ለዚህም ፡ ብዙ ፡ ማስረጃዎችን ፡ መጥቀስ ፡ ይቻላል ። በጎሳ ፡ ባህል ፥ ርስት ፡ ኹሉ ፡ የባላባቱ ፡ ነበር ፤ ***"ፊዎዳሊዝም"*** **፡ በኢትዮጵያ ፡ ነበር ፡ ቢባል ፥ በጎሳ ፡ ልማድ ፡ እንጂ ፡ በሀገር ፡ ሥሪት ፡ አልነበረም ። የዐምሐራ ፡ ሀገራዊ ፡ ሥርዐት ፡ የሰው ፡ ልጅን ፡ የነጻነት ፣ ራስን ፡ የመቻል ፡ መብቱን ፡ በማክበር ፥ የርስትን ፡ ሥርዐት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በጠቅላላው ፡ ሰጥቷል ። ጾታን ፣ ሃይማኖትን ፣ ማኅበረሰብን ፡ ሳይለይ ፥ ርስትን ፡ ለሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ኹሉ ፡ በሕግ ፡ አስከብሯል ።** ባርብቶ-ዐደርነትም ፡ ኾነ ፡ በለቀማ ፡ በሚተዳደሩ ፡ አካባቢዎች ፥ በጫካ ፡ ተሸፍኖ ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ መፈንጫ ፡ የነበረውን ፡ ጠፍ ፡ መሬት ፡ ጥሶ ፡ እና ፡ መንጥሮ ፣ ገምሶ ፡ እና ፡ ገልግሎ ፣ ዐይሞ ፡ እና ፡ አለስልሶ ፣ ዘርቶ ፡ እና ፡ ዐርሞ ፣ ዐጭዶ ፡ እና ፡ ከምሮ ፣ ወቅቶ ፡ እና ፡ እጐተራ ፡ ከትቶ ፡ ሕዝብን ፡ የመገበው ፡ የዐምሐራ ፡ ገበሬ ፥ ለሺሕ ፡ ዓመታት ፡ የካበተውን ፡ የግብርና ፡ ሟያውን ፡ ለኹሉም ፡ አስተምሮ ፥ ዛሬ ፡ አብዛኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በዕርሻ ፡ የሚተዳደር ፡ ኾኗል ። **የደርግ ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፥ በንኀለታዊ ፡ (nihilistic) ፡ የምልክዮሽ ፡ የጥፋት ፡ ምክር ፡ ተነሣሥቶ ፥** ***"መሬት ፡ ላራሹ"*** **፡ በሚል ፡ አማላይ ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ደጎኛውን ፡ የርስት ፡ ሥርዐት ፡ እስኪያጠፋው ፡ እና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ዛሬ ፡ እምናውቀው ፡ የድኽነት ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ በጪሰኝነት ፡ እስኪያነጥፈው ፡ ድረስ ፥ ኢትዮጵያ ፥ በርስት ፡ ሀገርነቷ ፥ በባለርስቶቹ ፡ ብዛት ፡ በዓለም ፡ ተወዳዳሪ ፡ አልነበራትም ።** ይህ ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፥ በ*"ብሔር-ብሔረሰብ ፡ ፖለቲካ"* ፡ ትውልዶች ፡ ከኢትዮጵያዊ ፡ ሥልጣኔያቸው ፡ ሳይወዱ ፡ በግዳቸው ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ማኅበረሰባዊ ፡ ልማዳቸው ፡ እንዲያንሱና ፥ በኢትዮጵያዊ ፡ ሥልጣኔው ፡ ጸንቶ ፡ የተገኘውን ፡ *"ጨቋኝ ፡ ዐምሐራ"* ፡ በሚል ፡ ጤቀኛ ፡ አባባል ፡ እየጠቈሙ ፥ ካለማው ፡ አካባቢ ፡ እንዲያባርሩት ፡ ይደረጋል ።

በቅርቡ ፡ የታዘብነውን ፡ ሌላ ፡ ማስረጃ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ እንጥቀስ ። በነሐሴ ፡ አጋማሽ ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ ላይ ፥ በለንደን ፡ ከተማ ፡ የዐማራ ፡ ድርጅቶችን ፡ ለማሰባሰብ ፡ በተጠራ ፡ ጉባኤ ፡ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ተወካይ ፡ ተገኝቶ ፡ የአንድነቱን ፡ መልእክት ፡ በማስተላለፍ ፦ *"በዚህ ፡ ሰዓት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አንድነት ፡ እና ፡ ነጻነት ፡ የሚዋደቁትን ፡ ወንድሞቻችንን ፡ እና ፡ እኅቶቻችንን ፡ ፋኖዎች ፡ በማመስገን ፡ እዠምራለኹ ፥ ..."* ፡ ሲል ፥ አዳራሹ ፡ ውስጥ ፥ ወደ ፡ ኋላ ፡ የተቀመጡ ፥ ከሦስት ፡ ያልበለጡ ፡ ወጣቶች ፦ *"ስለ ፡ ዐማራ ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለማውራት ፡ አይደለም ፡ እዚህ ፡ የተሰበሰብነው !"* በማለት ፡ ግራ ፡ የተጋባውን ፡ ሐሳብ ፡ አሰምተው ፡ ንግግሩ ፡ እንዲቋረጥ ፡ ጠየቁ ። የClint Eastwoodን ፡ የመሰለ ፡ ትልቅ ፡ ባርኔጣ ፡ እራሳቸው ፡ ላይ ፡ ደፍተው ፡ ጉባኤውን ፡ በሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ተሠይመው ፡ ያስተናብሩ ፡ የነበሩት ፡ ወጣት ፡ ኮሎኔልም ፥ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ተወካይ ፡ ንግግር ፡ ወዲያዉኑ ፡ እንዲቋረጥ ፡ አዘዙ ። ቀጥሎ ፥ የዐማራ ፡ ድርጅቶችን ፡ የሚያስተባብር ፡ *"ኮሚቴ"* ፡ አባላትን ፡ ጥቈማ ፡ እና ፡ ምርጫ ፡ እናካኺድ ፡ ተባለና ፥ ኮሎኔሉ ፡ የጥቈማውን ፡ መስፈርት ፡ ሲያብራሩ ፦ *"የምትጠቍሟቸው ፡ ሰዎች ፥ በኹለቱም ፡ የዘር ፡ ግንዶቻቸው ፡ ፍጹም ፡ ዐማራ ፡ መኾናቸውን ፡ እያረጋገጣችኹ ፡ ይኹን ፤ ካራቱ ፡ ክፍላተ ፡ ሀገር ፡ ከጐንደር ፣ ከጐዣም ፣ ከወሎ ፡ እና ፡ ከሸዋ ፡ መኾን ፡ አለባቸው ፤ ከዚህ ፡ ውጭ ፡ አንቀበልም ፡ ... ።"* ዐሉ ። ይገርማል ! በአውሮፓ ፡ ምድር ፥ በ21ኛው ፡ ምእትያ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ የፋሺስት ፡ አስተሳሰብን ፡ ከኢትዮጵያዊ ፡ አንደበት ፡ መስማቱ ፡ ያስደነግጣል ። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ መጠነኛ ፡ የአእምሮ ፡ ድኽነትን ፡ እና ፡ የትውልድ ፡ ተናቃላነትን ፡ እንዳመጣብን ፡ ቢታወቅም ፥ ይህን ፡ ጽንፍ ፡ የረገጠ ፡ አስተያየት ፡ ያሰሙ ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ወጣቶች ፡ እና ፡ በስተእርጅና ፡ የብሪታንያን ፡ ዜግነት ፡ የያዙ ፡ በጣት ፡ የሚቈጠሩ ፡ ትውልደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጡረተኞች ፥ ከብዙኃኑ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አስተሳሰብ ፡ ያፈነገጡ ፥ እንዲያውም ፡ የብዙኃኑን ፡ አስተያየት ፡ የተፃረሩ ፡ ናቸው ። ራሳቸው ፡ እየተፈራረቁ ፡ ሲናገሩ ፡ እንዳረጋገጡት ፦ *"ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ በጠራን ፡ ቍጥር ፥ የሚመጣልን ፡ ሰው ፡ ከ20 ፡ እና ፡ ከ30 ፡ አይበልጥም !"* እያሉ ፡ ደጋግመው ፡ አማርረዋል ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ነው ፡ በተባለበት ፡ ዘመን ፥ ዘር-ለዪ ፡ ከፋፋይ ፡ ስብከትን ፡ እየነዙ ፡ ማን ፡ እንዲመጣላቸው ፡ ይፈልጋሉ ፧ እንኳን ፡ ተማርኩ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

ያለውና ፥ ፊደል ፡ ያልቈጠረው ፡ ያገራችን ፡ ባላገርም ፡ እንኳ ፡ የሰውን ፡ ልክ ፡ ያውቃል ፤ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አክብሮት ፡ አለው ። ኢትዮጵያዊ ፡ ኹሉ ፥ ዐምሐራነትን ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብነት ፡ እንጂ ፣ እንደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ማንነት ፡ እንጂ ፣ እንደሀገር ፡ ባለቤትነት ፡ እንጂ ፣ እንደ ፡ *"ዘር"* ፡ አይቈጥረውም ። ይህ ፡ ኹሉ ፡ ባዕድ ፡ አስተሳሰብ ፡ የምልክዮሽን ፡ የ *"ከፋፍለኽ ፡ ግዛ"* ፡ ስልት ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ደባ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እንደመድማለን ። ርግጥ ፡ ነው ፥ ቀደም ፡ ሲል ፥ *"የትግሬ ፡ ማኅበር"* ፣ *"የኦሮሞ ፡ ማኅበር"* ፣ *"የሶማሌ ፡ ማኅበር"* ፣ *"የሲዳማ ፡ ማኅበር"* ፡ ... ፡ ወዘተርፈ ፥ በብሪታንያ ፡ ውስጥ ፡ እንዲቋቋም ፡ ሲደረግ ፥ ዐምሐራ ፡ ከኢትዮጵያዊነት ፡ ተለይቶ ፡ ወይ ፡ አንሶ ፡ ስለማይታይ ፥ ኹል ፡ ጊዜም ፡ ለዐምሐራ ፡ ኀይል ፡ የሚኾንለት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ማኅበረሰብ ፡ በሞላው ፡ ነው ።

*"ይህ ፡ ኹሉ ፡ ዐማራ ፡ ላይ ፡ ያነጣጠረ ፡ ዕልቂት ፡ ሲፈጸም ፡ ለውጭ ፡ መንግሥታት ፡ አቤት ፡ ያለ ፡ የዐማራ ፡ ድርጅት ፡ አልተገኘም ። ስለዚህ ፥ የዐማራ ፡ ድርጅት ፡ ብሎ ፡ ማደራጀት ፡ አለብን"* ፡ የሚል ፡ አመክንዮ ፡ ተደጋግሞ ፡ ይነገራል ። እውን ፥ መላው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በአንድነት ፡ ጮኾ ፡ ያልተሰማ ፥ በማኅበረሰብ ፡ ተከፋፍሎ ፡ ሊሰማ ?! ዘበት ። ችግሩ ፡ የሚመጣው ፡– *"ዐማራ ፡ ስንል ፡ ምን ፡ ማለታችን ፡ ነው ፧ "* ለሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ከሚሰጠው ፡ መልስ ፡ ነው ። ዐማራ ፡ ስንል ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ማለታችን ፡ ከኾነ ፥ ይህ ፡ ኹላችንንም ፡ ያስማማናል ፤ ዐማራነት ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነት ፡ ነው ፤ እንተባበራለን ። ባልቻ ፡ አባ ፡ ነፍሶ ፣ ዑመር ፡ ሰመተር ፣ በቀለ ፡ ወያ ፡ በትውልድ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ማኅበረሰብ ፡ ቢወለዱም ፥ በሀገራዊነት ፡ ከማንም ፡ ያላነሱ ፡ ዐማራዎች ፡ ናቸው ፤ እንዲሁም ፡ ገረሱ ፡ ዱኪ ፣ ዐሊ ፡ ኑር ፣ ጃገማ ፡ ኬሎ ፣ ዘርዓይ ፡ ድረስ ፣ ወዘተርፈ ። **ዐምሐራ ፡ *"ያራቱ ፡ ክፍላተ ፡ ሀገር"* ፡ የጐንደር ፣ የጐዣም ፣ የወሎ ፡ እና ፡ የሸዋ ፡ ተወላጆች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ ሊሉን ፡ የሚቃጡት ፡ ምልክዮሽ ፡ እና ፡ ጀሌዎቹ ፡ ናቸው ።** ሞያሌ ፡ እና ፡ ገምቤላ ፡ ብንወርድ ፣ ሀዋሳ ፡ እና ፡ ጂግጂጋ ፡ ጐራ ፡ ብንል ፥ ዛሬ ፡ የምንሰማው ፡ ዐማርኛ ፡ የዐዲስ ፡ አበባ ፡ ዐማርኛ ፡ ኾኗል ፤ ሀገራዊው ፡ ባህል ፡ በሚገባ ፡ ሠርጿል ፣ ተስፋፍቷል ፤ **ኹሉም ፡ በሀገራዊነት ፡ ተመሳስሏል ፥ ዐምሐራ ፡ ኾኗል ። የውልደት ፡ ነገር ፡ ቀርቷል ፤ የሚያዋጣው ፡ ሀገራዊነት ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ ኹሉም ፡ እኩል ፡ ተረድቶታል ።** ዛሬኮ ፡ ለኦሮሞ ፡ ነጻነት ፡ እንታገላለን ፡ የሚሉት ፡ ሎሬዎች ፥ አንድ ፡ ሳይቀር ፥ ኹሉም ፡ ከኦሮሞ ፡ ማኅበረሰብ ፡ በከፊል ፡ የተገኙ ፡ እንጂ ፥ *"ቱባ"* ፡ ኦሮሞዎችም ፡ አይደሉ ። **በ *"ዘር"* ፣ በጎሳ ፣ በውልደት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ማኅበረሰብነት ፡ እየሟሸሸ ፡ የሚኼድ ፥ በርትዕ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ዐምሐራነት ፡ (ነጻ ፡ ሕዝብነት) ፡ ወይም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነት ፡ ደግሞ ፡ ኹሉንም ፡ በውዴታ ፡ እያዋሐደ ፣ እየዳበረ ፣ እየፋፋ ፣ እየሰፋ ፡ የሚኼድ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብና ፡ ስለ ፡ መኾኑ ፡ ማንኛችንም ፡ የምንስማማበት ፡ እውነት ፡ ኾኗል ።** በኦሮሞ ፡ *"ክልል–ተብዬው"* ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፥ አላንዳች ፡ በቀርታ ፥ በእናትም ፡ በአባትም ፡ ከኦሮሞ ፡ ማኅበረሰብ ፡ ብቻ ፡ እወለዳለኹ ፡ የሚለው ፡ ነዋሪ ፡ መጠን ፡ ከ 5% ፡ (ከዐምስት ፡ በመቶ) ፡ እንደማይበልጥ ፡ በአኃዝ ፡ ተረጋግጧል ። የኦሮሞ ፡ *"ክልል–ተብዬው"* ፡ የነዋሪ ፡ ብዛት ፡ 25 ፡ ሚልዮን ፡ ይገመታል ። ከዚህ ፡ ውስጥ ፡ በእናትም ፡ በአባትም ፡ *"ኦሮሞ ፡ ነኝ"* ፡ ባዩ ፡ ከ 2 ፡ ሚልዮን ፡ አይበልጥም ፤ ከሚሶ ፡ እስከ ፡ ግማሽ ፡ በግማሽ ፡ ደግሞ ፡ ከ *"ኦሮሞ"* ፡ ማኅበረሰብ ፡ አይወለድም ፥ ቀሪው ፡ ከፊል ፡ ኦሮሞ ፡ ነው ። እንደ ፡ Wikipedia ፡ ያሉ ፡ ማወራኛዎች ፡ ግን ፥ የሚያስተጋቡት ፡ እና ፡ የሚነዙት ፡ እጅጉን ፡ የተጋነነ ፡ የ *"ፕሮፐጋንዳ"* ፡ አኃዝ ፥ ብዙዎችን ፥ በተለይ ፡ *"ለኦሮሚያ ፡ ታላቅነት"* ፡ ደፋ ፡ ቀና ፡ የሚሉትን ፡ የዋሆች ፡ ጉም ፡ ሳያስዘግናቸው ፡ አልቀረም ። እምድር ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ እውነት ፡ ዕጥጥ ፡ ሙጥጥ ፡ ብሎ ፡ የታያቸው ፡ ዕለት ፡ ክፉኛ ፡ ይሣቀቃሉ ። ይህ ፡ የሚያሳዝንም ፡ የሚያስደስትም ፡ ጕዳይ ፡ አይደለም ፤ እንደ ፡ እውንነቱ ፡ ልንቀበለውና ፡ ልናከብረው ፡ የሚገባ ፡ የሀገር ፡ ግንባታ ፡ ኺደት ፡ ነው ።

የኹሉም ፡ ማኅበረሰብ ፡ ዕጣ ፡ ፈንታ ፡ በሀገራዊነት ፡ መዋሐድ ፡ ኾኗል ። **ጕዳዩ ፡ *"ከዘር ፡ መባረዝም"* ፡ በላይ ፡ የሥልጣኔ ፡ ምርጫ ፡ ኾኗል ። ሀገር ፡ በርትዕ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንደ ፡ መሠራቱ ፡ መጠን ፥ የሀገራዊነት ፡ ህልውናም ፡ የርትዕ ፡ ህልውና ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በኹሉም ፡ ነዋሪዎች ፡ ዘንድ ፡ ይወደዳል ፥ ይመረጣልም ።** ዛሬ ፥ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነትን ፡ ወይም ፡ ዐምሐራነትን ፡ በውዴታው ፡ የሚያቅፈው ፡ ነዋሪ ፡ ብዛት ፡ ልቆ ፡ ተገኝቷል ፤ ወላጆች ፡ ለልጆቻቸው ፡ በውዴታቸው ፡ የሚሰጡትን ፡ መጠሪያ ፡ ስም ፡ ማየት ፡ ይበቃል ። ይህን ፡ የመሰለው ፡ አካኼድ ፡ ደግሞ ፥ በኢትዮጵያ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ በሌሎች ፡ ሀገሮችም ፡ ይከናወናል ። እንደ ፡ ፍራንስም ፡ ባሉ ፡ የቈዩ ፡ ሀገሮች ፥ ከመቶ ፡ ከኹለት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ በሀገርነት ፡ በተዋቀሩትም ፡ እንደ ፡ የተባበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ ኹነቶች ፡ (United States of America) ፡ ባሉ ፡ ዘመናውያን ፡ ሀገሮች ፥ ሀገራዊነት ፡ የሳባቸው ፥ የውጭ ፡ ዜጎች ፡ እንኳ ፡ ተንጋግተው ፡ በመጤነት ፡ እየገቡ ፥ ወቅቱን ፡ ጠብቀው ፡ የሀገራዊነት ፡ ለውጥ ፡ መጠየቂያን ፡ እያስገቡ ፡ እና ፡ ፈቃድን ፡ እያገኙ ፥ ዘራቸው ፣ ሃይማኖታቸው ፡ ሳይጠየቅ ፥ በመረጡት ፡ ሀገራዊነታቸው ፡ ሰላማዊ ፡ እና ፡ የተደላደለ ፡ ኑሯቸውን ፡ ይመራሉ ። በዚህ ፡ ረገድ ፥ ኢትዮጵያ ፡ የ 3000 ፡ ዘመን ፡ ቅድሚያ ፡ ያላት ፡ ሥልጡን ፡ ሀገር ፡ ነበረች ፥ የዛሬን ፡ አያድርገውና ።

"**ኢንተርኔት**" ፡ የተባለው ፡ የመገናኛ ፡ መርበብት ፦ *"ላይኳን ፡ ፕሬስ ፡ አድርጉ ፡ ... ፤ ሰብስክራይብ ፡ እና ፡ ሼር ፡ ማድረግን ፡ አትርሱ ፡ ... ፤ "* እያለ ፥ **በታላቅ ፡ ሰፌዱ ፥ ብዙኃኑን ፡ እያንገዋለለ ፡ እና ፡ እያጓለበ ፥ እያንጠረጠረ ፡ እና ፡ እያንቀረቀበ ፥ የሰው ፡ ልጅን ፡ በዐይነት ፡ በዐይነቱ ፡ ለይቶ ፥ ጽንፍ ፡ የያዙለትን ፡ ጥቂቶች ፡ አበጥሮ ፡ በማደራጀት ፥ ለፈለገው ፡ ዐላማ ፡ ያስሰልፋቸዋል ፥ እንደ ፡ ፍላጎቱም ፡ ያውላቸዋል ።** *"ዐማራን ፡ በዘር ፡ እናደራጀው"* ፡ የሚለው ፡ ሤራ ፡ የምልክዮሽ ፡ ኀይሎች ፡ ለ *"ከፋፍለኽ ፡ ግዛ"* ፡ ስልታቸው ፡ የሚያሤሩት ፡ ሤራ ፡ ስለ ፡ መኾኑ ፡ በቂ ፡ ማስረጃን ፡ ጠቅሰናል ። በቀላሉ ፡ ወደ ፡ ጽንፍ ፡ የመጡላቸውን ፡ ጥቂቶች ፡ የዋሃንን ፡ ይዘው ፥ እንሆ ፦ *"ዐማራን ፡ በዘር ፡ እናደራጀዋለን !"* ፡ ባሉት ፡ መሠረት ፥ ግፋ ፡ ቢል ፡ 50 ፡ ወይ ፡ 60 ፡ የሚኾኑ ፡ ሰዎችን ፡ በዐማራ ፡ *"ዘርነት"* ፡ በእየምክንያቱ ፡ እያሰለፉ ፥ የኢትዮጵያውያንን ፡ *"መከፋፈል"* ፡ በገቢር ፡ ያሳዩበታል ፤ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ከታሪክ ፡ አለመማር ፡ ይባላል ። ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረችበት ፡ ወቅት ፥ የኦሮሞ ፡ ማኅበረሰብ ፡ አባላት ፡ ዐማራን ፡ እንዲፈጁላት ፥ በሸዋም ፣ በወለጋም ፣ በጂማም ፡ የጦር ፡ መሣሪያን ፡ እያደለች ፡ ስትገፋፋቸው ፥ በተወሰነ ፡ ደረጃ ፥ የሰብእና ፡ ሕጸጽ ፡ የነበረባቸው ፡ ጥቂት ፡ ድኩማን ፥ ይህን ፡ ርኩስ ፡ ግብር ፡ ቢፈጽሙላትም ፡ ቅሉ ፥ ማኅበረሰቡ ፡ ግን ፡ በጠቅላላው ፡ ይህን ፡ አድራጎት ፡ አነውሮ ፥ ካርበኞች ፡ ጐን ፡ በመሰለፍ ፥ እንደ ፡ እነጃገማ ፡ ኬሎ ፡ ያሉትን ፡ ዠግኖች ፡ ልጆቹን ፡ ለኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነት ፡ ድል ፡ አበርክቷል ። ዛሬም ፡ የተለየ ፡ ነገር ፡ አናይም ። **ትላንት ፡ በሀገራዊነቱ ፡ በኢጣሊያ ፡ ፋሺስት ፡ ተለይቶ ፡ የተጠቃው ፡ ሀገራዊው ፡ ሕዝብ ፡ ዐምሐራ ፥ ባልቃሻነት ፦ *"ኢትዮጵያ ! ኢትዮጵያ ! ማለቱ ፡ አልበጀኝም ፤ ኢትዮጵያ ፡ ትቅርብኝ ፤ ልገንጠል"* ፡ እንዳላለ ፡ ኹሉ ፥ ዛሬም ፡ በእጅ ፡ አዙር ፥ በምልክዮሽ ፡ ቅጥረኞች ፡ ኀይሎች ፡ ተለይቶ ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚጠቃው ፡ ሀገራዊው ፡ ሕዝብ ፡ ዐምሐራ ፥ ከኢትዮጵያ ፡ የጠበበ ፡ ሀገር ፡ እንደሌለው ፡ አኹንም ፡ በገቢር ፡ አስመስክሯል ፥ ወደ ፡ ፊትም ፡ ያስመሰክራል ።**

በ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ ምልክዮሽ ፡ በበቀል ፡ መልክ ፡ ከደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ ነቅሎ ፥ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ግዘፈ ፡ አካል ፡ ሠርቶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ የተከለብን ፡ የ *"አፓርትሀይድ"* ፡ ምዉት ፡ ሥርዐት ፥ በሚልዮን ፡ ለሚቈጠሩ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሞት ፡ እና ፡ ስደት ፡ ምክንያት ፡ ኾኗል ፣ ሀገርንም ፡ ላጠቃላይ ፡ ክሳራ ፡ ሲዳርግ ፡ ቈይቷል ። በቀል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነውና ፥ አንበቀልም ፤ እግዚአብሔር ፡ በጊዜው ፡ ይበቀልልናል ። ነገር ፡ ግን ፥ **ከምልክዮሽ ፡ ሤራ ፡ ራሳችንን ፡ መጠበቅ ፣ የ *"አፓርትሀይድ"*ንም ፡ ጥንብ ፡ መቅበር ፡ የእኛ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ታሪካዊ ፡ ኀላፊነት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በዐምሐራነት ፡ የሚመራውን ፡ ትግል ፡ ኹላችን ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በአንድነት ፡ ልንተባበረው ፡ ሥልጡንሕዝብናችን ፡ ያስገድደናል ።**

**ኹሉም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዐምሐራ ፡ ነው !**

ድል ፡ ለዐምሐራ !

ድል ፡ ለኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነት !

ድል ፡ ለሥልጡንሕዝባዊት ፡ ኢትዮጵያ ፨

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡
ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።
ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።